የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፰
አዲስ አበባ ታህሳስ ፳፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No. 8
ADDIS ABABA, 3rd January 2017

ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺፭/፪ሺ፱ ዓ.ም

የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ)ደንብ...ገፅ ፱ሺ፬፻፹፭
ሰንጠረዥ...............................ገፅ ፱ሺ፬፻፺፬

CONTENT

Council of Ministers Regulation No.395/2017

Road Transport Traffic Control Council of Ministers (Amendment) Regulation..................page 9485
Schedule..................page 9494

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺፭/፪ሺ፱

## የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብን ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፯ አንቀጽ ፭ እና በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፳፰ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

**፩.አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፫፻፺፭/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪.ማሻሻያ**

የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፰/፪ሺ፫ እንደሚከተለው ተሻሽሏል:-

፩/ የደንቡ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፲፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንኡስ አንቀጽ (፲፪) ተተክቶ፣ሌሎች አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፲፫) እና

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 395/2017

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO AMEND ROAD TRANSPORT TRAFFIC CONTROL REGULATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No.916/2015 and Article 28 of the Transport Proclamation No.468/2005.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Road Transport Traffic Control Council of Ministers (Amendment) Regulation No.395/2017."

**2. Amendment**

The Road Transport Traffic Control Council of Ministers Regulation No.208/2011 is hereby amended as follows:

1/ sub-article (12) of Article 2 of the Regulation is deleted and replaced by the following new sub-article (12) and other new sub-articles (13) and (14) are added following sub-article (12) and the

(፲፬) ተጨምረው ነባሮቹ ንዑስ አንቀጾች እንደቅደም ተከተላቸው ከንዑስ አንቀጽ (፲፭) እስከ (፴፭) ሆነው ተሸጋሽገዋል:-

"፲፪/ 'ትራፊክ ተቆጣጣሪ' ማለት የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መከበራቸውን ለመቆጣጠር እና የትራፊክ ፍሰትን ለማስተናበር አግባብነት ባለው ሕግ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሲሆን ትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ ወይም የትራንስፖርት ተቆጣጣሪ በሚል ይታወቃል፤

፲፫/ 'ትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ' ማለት የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መከበራቸውን ለመቆጣጠር እና የትራፊክ ፍሰትን ለማስተናበር አግባብነት ባለው ሕግ ሥልጣን የተሰጠው የፖሊስ አባል ነው፤

፲፬/ 'ትራንስፖርት ተቆጣጣሪ' ማለት የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መከበራቸውን ለመቆጣጠር በተለይም በመንገድ ላይ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችን የቴክኒክ ብቃት እንዲያረጋግጥና ከትራንስፖርት አስተዳደር ጋር በተያያዘ የወጡ መመሪያዎችን አፈፃፀም ለመቆጣጠር አግባብ ባለው አካል ሥልጣን የተሰጠው ሰው ነው፤"

፪/ የደንቡ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፴) በዚህ ደንብ በንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተሸጋሸገው ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፴) ተተክቷል።

"፴/ የመንገድ ማመላከቻ' ማለት ተላላፊዎችን ለማቆምና ለማስተላለፍ የሚያገለግል በእጅ፣ በመካኒክ፣ ወይም በኤሌክትሪክ ሀይል አማካኝነት በመለዋወጥ የሚሰጥ ምልክት ነው፤"

፫/ የደንቡ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ(፪) ፊደል ተራ (ሀ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ሀ) ተተክቷል፤

"ሀ) ከአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪ አሽከርካሪ

existing sub-articles are renumbered as sub-article (15) to (35), respectively:

"12/ 'traffic controller' means a recognized controller empowered by an appropriate law to control traffic flow and enforce the provisions of this Regulation; and is known as traffic controller police or transport controller;

13/ 'traffic controller police' means a member of police recognized as controller and empowered by appropriate law to control traffic flow and enforce the provisions of this Regulation;

14/ 'transport controller' means a person recognized as controller and empowered by appropriate law to control the technical competence of vehicles and enforcement of directives related to transport administration;"

2/ sub-article (30) of Article 2 of the Regulation as renumbered under sub-article (1) of this Regulation is deleted and replaced by the following new sub-article (30):

"30/ 'road signal' means any signal operated manually, mechanically or electrically, by which traffic is alternately directed to stop, take direction and to proceed;"

3/ Paragraph (a) of sub-article (2)of Article 5 of the Regulation is deleted and replaced by the following new paragraph (a):

"a) Except emergency service vehicle driver, it is forbidden to any driver to call a telephone or

በስተቀር ማንኛውም አሽከርካሪ ተንቀሳቃሽ ስልክን ወይም ሬዲዮ በእጁ ይዞ እየተነጋገረ፣ አጭር መልዕክት እየፃፈ፣ እየላከ፣ ወይም እያነበበ ማንኛውንም ተሽከርካሪ ማሽከርከር የለበትም።"

፬/ የደንቡ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፭) ርዕስና ፊደል ተራ (ሀ) ተሰርዘው በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ርዕስና ፊደል ተራ (ሀ) ተተክተዋል፤

"፭/ የመንገድ ምልክቶች፣ ማመላከቻዎች፣ እና በትራፊክ ተቆጣጣሪ ስለሚሰጡ ምልክቶች:-

ሀ) በመንገድ የሚጠቀም ማንኛውም ሰው በመንገድ ምልክቶች፣ በማመላከቻዎች እና በትራፊክ ተቆጣጣሪ አማካኝነት የሚሰጠውን ትዕዛዝ መፈጸም አለበት።"

፭/ በደንቡ ከአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፰) ፊደል ተራ (ሐ) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (መ) ተጨምሯል:-

"መ) ማንኛውም አሽከርካሪ የፊትና የኋላ ሠሌዳ የሌለውን ተሽከርካሪ ማሽከርከር የለበትም።"

፮/ የደንቡ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፱) ፊደል ተራ (ለ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ለ) ተተክቷል:-

"ለ) ማንኛውም ሰው በእንስሳ ላይ ተቀምጦ ሲሄድ፣ ወይም እንስሳን እየነዳ ወይም እየጎተተ ሲሄድ፣ ወይም በእንስሳ የሚንቀሳቀስ ጋሪን ወይም ሰረገላን እየነዳ በመንገድ ላይ በሚሄድበት ጊዜ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት።"

፯/ በደንቡ ከአንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፫) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተጨምሯል:-

"፬/ በተሽከርካሪ ወይም በእግረኛ መንገድ ላይ ወይም ፍሳሹ ወደ እግረኛ ወይም ወደ ተሽከርካሪ መንገድ በሚገባበት ስፍራ ላይ ተሽከርካሪውን ማጠብ ወይም ማሳጠብ የለበትም።"

communicate through radio either by handling it or writing short notice, sending message or reading texts while driving any vehicle."

4/ the sub-article title (5) and paragraph (a) of Article 5 of the Regulation are deleted and replaced by the following new sub-article title (5) and paragraph (a):

"5/ Road Signs, Markings, and Signals given by Traffic Controller:

a) any person using road shall implement road signs, markings and signal and instructions given by Traffic Controller."

5/ The following new paragraph (d) is added following paragraph (c) of sub-article (8) of the Regulation:

"d) a vehicle driver is forbidden to drive a vehicle lacking front and back plate number."

6/ Paragraph (b) of sub-article (9) of Article 5 of the Regulation is deleted and replaced by the following new paragraph (b):

"b) Any person moving by sitting on animals' back or driving animals or towing animals or driving animals which tow any carriage shall take necessary care."

7/ the following new sub-article (4) is added after sub-article (3) of Article 8 of the Regulation:

"4/ not wash or cause washing of vehicle on the pedestrian's road or on a vehicle's road; or on a place that may cause liquid to flows into the pedestrian's road or on a vehicle's road."

፰/የደንቡ አንቀጽ ፲፱ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል:-

"፩/ ማንኛውምአሽከርካሪ ከመጠምዘዙ፣ አቅጣጫ ከመለወጡ፣ ፍጥነት ከመቀነሱ ወይም ከማቆሙ አስቀድሞ በከተማ ክልል ውስጥ በ ፳፭ ሜትር እና ከከተማ ክልል ውጪ በ፶ ሜትር ርቀት ላይ ለሌሎች የመንገድ ተጠቃሚዎች ጉልህ ሆኖ ሊታይ የሚችል የማስጠንቀቂያ ምልክት መስጠት አለበት።"

፱/ በደንቡ ከአንቀጽ ፳፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተጨምሯል:-

"፫/ ማንኛውም አሽከርካሪ ባለ አራት ጎን ቢጫ የትራፊክ መስመር በተቀባ መስቀለኛ መንገድ ላይ በተቃረበ ጊዜ ወደተቀባው የትራፊክ መስመር ቀድሞ ለገባው አሽከርካሪ ቅድሚያ መስጠት አለበት።"

፲/ በደንቡ ከአንቀጽ ፴፱ ንዑስ አንቀጽ (፫) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተጨምሯል፤

"፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከተሽከርካሪው የመጫን አቅም በላይ የሆነ መቀመጫ ወይም ማንኛውንም እንደመቀመጫ የሚያገለግል ነገር በተሽከርካሪው ላይ ተገጥሞ ወይም ተቀምጦ ሲያገኝ የትራንስፖርት ተቆጣጣሪው ይኸው እንዲነሳ ወይም ከተሽከርካሪው ላይ እንዲያወርድ አሽከርካሪውን ለማዘዝና ይኸው እስኪፈፀም ድረስም ተሽከርካሪው እንዲቆም ለማድረግ ይችላል።"

፲፩/ የደንቡ አንቀጽ ፵ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል:-

8/ sub-article (1) of Article 19 of the Regulation is deleted and replaced by the following new sub-article (1):

"1/ any driver before turning, changing direction, lowering speed or parking, shall give a clear warning signal at a distance of 25 meter within a town and 50 meter outside a town to other road users."

9/ The following new sub-article (3) is added after sub-article (2) of Article 24 of the Regulation:

"3/ Any driver of a vehicle approaching a marked rectangular yellow traffic line at intersectional road shall cede priority to cross the intersection to any driver of a vehicle that has already entered the intersection."

10/ The following new sub-article (4) is added after sub-article (3) of Article 39 of the Regulation:

"4/ Without prejudice to sub-articles (2) and (3) of this Article, in excess of loading capacity of a vehicle if a seat or anything serves as a seat is fixed with a vehicle or put in a vehicle, transport controller can order the driver to take off or to unload such seat and order the driver to stop the vehicle until he implements the given order."

11/ sub-article (2) of Article 40 of the Regulation is deleted and replaced by the following new sub-article (2):

"፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕድሜያቸው ከ ፲፫ ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናትን በአሽከርካሪው ጎን በሚገኘው የመኪናው የፊተኛው ክፍል ማስቀመጥ የለባቸውም።"

፲፪/ የደንቡ አንቀጽ ፶ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተተክቷል:-

"፬/ ማንኛውም የሞተር ብስክሌት አሽከርካሪ በሞተር ብስክሌቱ ላይ ዕቃን ለመጫን ተብሎ ከተሰራለት የዕቃ መጫኛ ሳጥን ውጪ ማናቸውንም ዓይነት ጭነት መጫን ወይም ከአንድ ሰው በላይ ማሳፈር የለበትም።"

፲፫/ የደንቡ ክፍል አስራ አንድ ርዕስ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ርዕስ ተተክቷል:-

"ክፍል አሥራ አንድ
የመንገድ ምልክቶች እና ማመላከቻዎች"

፲፬/ የደንቡ አንቀጽ ፷፫፣ ፷፬ እና ፷፭ ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ አንቀጾች ፷፫፣ ፷፬ እና ፷፭ ተተክተዋል፤

"፷፫. በአንድ ዓይነት የመንገድ ምልክትና ማመላከቻ ስለመጠቀም

ትራፊክን ለመቆጣጠር ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዘው በሚገኙት እና ወደፊት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ሥራ ላይ እንዲውሉ በሚደረጉ የመንገድ ምልክቶች እና ማመላከቻዎች ካልሆነ በስተቀር በሌላ የመንገድ ምልክት ወይም ማመላከቻ መጠቀም የተከለከለ ነው።

፷፬. የመንገድ ምልክትና ማመላከቻ መትከልና ማንሳት

ባለስልጣኑ የመንገድ ምልክቶችና ማመላከቻዎች እንዲተከሉ፣ እንዲታደሱ፣ እንዲጠገኑ፣ እንዲለወጡ ወይም እንዲነሱ የማድረግ ስልጣን ይኖረዋል።

"2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article, minors below 13 years age are not allowed to sit in the front seat of the vehicle near to a driver."

12/ sub-article (4) of Article 50 of the Regulation is deleted and replaced by the following new sub-article (4):

"4/ no driver of a motorcycle may load goods on a compartment other than those allowed to load on; or carry more than one passenger."

13/ Part Eleven of the Regulation's title is deleted and replaced by the following new title.

"PART ELEVEN
ROAD SIGNS AND MARKINGS"

14/ Article 63, 64 and 65 of the Regulation are deleted and replaced by the following new Article 63, 64 and 65:

"63. Use of One Road Sign and Markings

It is prohibited to use another road sign and markings other than those road signs and markings annexed as schedule to this Regulation and signs and markings may be prescribed by appropriate law in the future to control traffic.

"64. Installing and Removing Road Signs and Markings

The Authority shall have the power to install, renew, maintain, change or remove the road signs and markings.

፷፭. <u>የመንገድ ምልክቶችንና ማመላከቻዎችን ማኖር ክልክል ስለመሆኑ</u>

፩/ በዚህ ደንብ የተፈቀደላቸው ወይም ወኪሎቻቸው ካልሆኑ በስተቀር ማንኛውም ሰው በማንኛውም መንገድ ላይ ወይም በማንኛውም መንገድ አጠገብ የመንገድ ምልክት ወይም ማመላከቻ ወይም እንደ መንገድ ምልክትና ማመላከቻ ያለ ወይም የመንገድ ምልክት ወይም ማመላከቻ መስሎ የሚያሳስት ማናቸውንም ምልክት ወይም ማመላከቻ ማድረግ፣ ማቆም፣ ወይም መጠቀም የተከለከለ ነው።

፪) ማንኛውንም የመንገድ ምልክትና ማመላከቻ ማንሳት፣ ማበላሸት፣ ከቆመበት ማዛወር፣ መለወጥ፣ ወይም በማናቸውም አኳኋን በግልፅ እንዳይታይ ወይም እንዳይነበብ ማድረግ የተከለከለ ነው።"

፲፭/ በደንቡ አንቀጽ ፹፭(፩) መሠረት ከደንቡ ጋር ተያይዞ የነበረው ሠንጠረዥ 'ለ' ተሰርዞ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው አዲስ ሠንጠረዥ 'ለ' ተተክቷል።

፲፮/ የደንቡ አንቀጽ ፹፭ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፹፭ ተተክቷል:-

"፹፭. <u>በደንብ ተላላፊዎች ላይ ስለሚጣል ቅጣት</u>

፩/ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም አሽከርካሪ ወይም እግረኛ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው "ሠንጠረዥ ለ" መሰረት ይቀጣል።

፪/ የትራፊክ ተቆጣጣሪ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎችን የተላለፈን አሽከርካሪ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድን ጠይቆ በመቀበል ላጠፋው ጥፋት

**65.<u>Prohibition of Putting Road Signs and Markings</u>**

1/ no person shall put, erect or use road signs and markings or any fabrication of road signs and markings or any signs and markings looks like on road or near road except those who are licensed or their agents in accordance with this Regulation.

2/ no person may remove, damage, displace, change or to oblique from spectacle in any manner or make road signs and markings unreadable."

15/ Schedule 'B' attached with the Regulation in accordance to Article 85 (1) is deleted and replaced by the new Schedule 'B' attached herewith.

16/ Article 85 of the Regulation is deleted and replaced by the following new Article 85:

**"85. <u>Penalty on Regulation violators</u>**

1/ Any driver or pedestrian who violates the provisions of this Regulation shall be punished in accordance with the Schedule 'B' of this Regulation.

2/ A traffic controller shall request and take driving qualification license from a vehicle driver who violates the provisions of this Regulation and give appropriate charge letter which

የሚገባውን ቅጣት እንዲፈፅም የሚያዝ የቅጣት ወረቀት ይሰጠዋል።

፫/ የትራፊክ ተቆጣጣሪ ወይም በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ሌላ ሰው የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የተላለፈን እግረኛ ወይም ሌላ ማናቸውም ሰው ላጠፋው ጥፋት የሚገባውን ቅጣት እንዲፈፅም የቅጣት ወረቀት ይሰጠዋል፤ ዝርዝር አፈፃፀሙ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሰረት የቅጣት ወረቀት የተሰጠውና በተሰጠው የቅጣት ወረቀት ተገቢነት ላይ ቅሬታ ያደረበት ማንኛውም ሰው:-

ሀ) በሁለት የሥራ ቀናት ውስጥ የቅጣት ወረቀቱን ለሰጠው የትራፊክ ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት ቅሬታውን ለማቅረብ ይችላል፤

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) መሰረት ባቀረበው ቅሬታ ላይ በተሰጠው ምላሽ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው አግባብነት ላለው አካል ውሳኔውን ባወቀ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለማቅረብ ይችላል።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሰረት እንደቅደም ተከተሉ ቅጣት የተጣለበት አሽከርካሪ ወይም ማንኛውም ሰው በንዑስ አንቀጽ (፬) በተደነገገው መሰረት ቅሬታውን አቅርቦ ቅጣቱን ካላሻረ በስተቀር የተጣለበትን ቅጣት በአስር የሥራ ቀናት ውስጥ መክፈል አለበት።

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፭) መሰረት በአስር የሥራ ቀናት ውስጥ የተጣለበትን

commands to pay fines.

3/ A traffic controller or other legally authorized person shall give appropriate charge letter to a pedestrian or any other person who violates the provisions of this Regulation; the detail implementation of which shall be determined by the directive to be issued by the Authority.

4/ any person who receives charge letter to pay fine pursuant to sub-article (2) and (3) of this Article, but has a complaint on the penalty :

a) can lodge his complaint within two working days to the Office of Traffic Controller who provided him with a letter of charge to pay penalty;

b) any person if dissatisfied with decision given to him in accordance with paragraph (a) of this sub-article, can lodge his complaint to the head of the concerned authorized body within five working days.

5/ any driver and pedestrian fined in accordance with sub-articles (2) and (3), respectively, shall pay the penalty within 10 working days, unless he reverses his penalty through complaint lodged in accordance with sub-article (4) of this Article.

6/ If a driver fined does not pay the penalty within 10 working days in accordance with sub-article (5) of this Article, he

ቅጣት ያልከፈለ አሽከርካሪ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው "ሠንጠረዥ ለ" ተራ ቁጥር (፪)(ሐ) መሰረት ተጨማሪ ቅጣትና የጥፋት ሪከርድ ይያዝበታል፤ ከአሽከርካሪ ውጪ ቅጣት የተጣለባቸውን ሰዎችን የሚመለከተው ተመሳሳይ አፈፃፀም ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) የተደነገገው ቢኖርም የተጣለበት ቅጣት የከፈለ ማንኛውም አሽከርካሪ ቅጣቱን በከፈለ በሰላሳ ቀናት ውስጥ የተጣለበት ቅጣት እንዲሰረዝለት ቅሬታውን ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ለማቅረብ ይችላል፤በሚኒስቴሩ የሚሰጠውም ውሳኔ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሆናል።

፰/ የትራፊክ ተቆጣጣሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት ከአሽከርካሪው ላይ የተቀበለውን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሽከርካሪው ከየት መቀበል እንደሚችል ማስረዳት እና በሁለት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ በአቅራቢያው ለሚገኘው አግባብነት ላለው አካል ማስረከብ አለበት።

፱/ በዚህ አንቀጽ መሰረት በሚጣል ቅጣት የሚመዘገብ የጥፋት ነጥብ በሪከርድነት ተመዝግቦ የሚቆየው ለአንድ ዓመት ብቻ ይሆናል።"

፲፯/ ከደንቡ አንቀጽ ፹፭ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀጾች አንቀጽ ፹፮ እና ፹፯ ተጨምረው ነባሩ አንቀጽ ፹፮ አንቀጽ ፹፰ ሆኖ ተሸጋሽጓል:-

"**፹፮.<u>የትራፊክ ተቆጣጠሪዎች ስለሚፈፅሙት ጥፋት</u>**

፩/ ማንኛውም የትራፊክ ተቆጣጣሪ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ሲያስፈፅም ከአድሎ

shall be subject to additional penalty and to be recorded in punishment list pursuant to Schedule 'A' number (2)(C) attached herewith this Regulation. With regard to person other than driver, similar compliance shall be determined by a directive to be issued by the Authority.

7/ Notwithstanding the provision of sub-article (5) of this Article any driver who paid his fine penalty can lodge his complaint on the penalty to the Ministry of Transport for cancelation within 30 days; the decision to be given by Ministry shall be the final administrative decision.

8/ In accordance with sub article (2) of this Regulation A traffic controller who receives driving qualification license from a driver shall notify to the driver from where he can collect his license and deliver the license to the nearby concerned body within two consecutive working days.

9/ The fine imposed for violation of traffic Regulations pursuant to this Article shall enter in the judgment register and stay valid for one year as a record.

17/ The following new Articles 86 and 87 are added after Article 85 of the Regulation and the existing Article 86 of the Regulation is renumbered as Article 88:

"**86.<u>Offences Committed by Traffic Controllers</u>**

1/ Any traffic controller who enforces the provisions of this Regulation shall

በፀዳ እና ሰብዓዊ መብቶችን ባከበረ ሁኔታ መሆን ይኖርበታል።

፪/ ማንኛውም የትራፊክ ተቆጣጠሪ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ሲያስፈፅም ጥፋት የፈፀመ ስለመሆኑ የትራፊክ ተቆጣጣሪው መሥሪያ ቤት እምነት ያደረበት እንደሆነ በሌላ አግባብነት ባለው ሕግ የሚጠየቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 'ሐ' መሰረት ከትራፊክ ተቆጣጣሪነት ሥራ እንዲነሳ ይደረጋል።

**፹፯. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

ሚኒስቴሩ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።"

፲፰/ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ 'ሀ'ላይ የተገለፀው የመንገድ ላይ ቀብ ከደንቡ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 'ሀ' ተራ ቁጥር ፬ የመንገድ ላይ ቀቦች (መስመሮች) በሚለው ሠንጠረዥ መጨረሻ ላይ አዲስ የመንገድ ምልክት ሆኖ ተጨምሯል።

**፫.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

፩/ ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም፣ ለአሽከርካሪው የሚጠቅም ሆኖ ሲገኝ ይህ ደንብ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በተፈፀመ ጥፋት የተመዘገቡ የጥፋት ሪከርድ ነጥቦች በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሰረት ተስተካክለው ተፈፃሚ ይሆናሉ።

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፳፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

ኃይለማርያም ደሳለኝ

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

enforce them impartiality and without violating human rights.

2/ If a Traffic Control Office believes that a traffic controller has committed offence while enforcing the provisions of this Regulation, without prejudice to his liability in accordance with appropriate law, shall remove him from his traffic controlling duty in accordance with Schedule 'C' of this Regulation.

"**87. <u>Power to Issue a Directive</u>**

The Ministry of Transport may issue directive to enforce the provisions of this Regulation."

18/ The Road Marking prescribed on Schedule 'A' attached herewith this Regulation is added as road marking at the end of Schedule 'A' number 4 as new road sign.

**3. <u>Effective Date of the Regulation</u>**

1/This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

2/Notwithstanding sub-article (1) of this Article, if it is favorable to the driver, for an offence committed before coming into force of these Regulations, the record points of offences can be corrected to make effective in accordance with the provisions of this Regulation.

**Done at Addis Ababa, this 3rd day of January, 2017**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

## ሠንጠረዥ "ሀ"

| 4. የመንገድ ላይ ቅቦች (መስመሮች) | | 4. ROAD MARKINGS |
|---|---|---|
| መሀል ላይ ሳትቆም ልታልፈው የምትችል መሆኑን ካላረጋገጥክ በስተቀር ቢጫ ቀለም ወደተቀባበት የመንገድ ክፍል መግባት የለብህም:: |  | You must not enter the yellow box junction unless you can cross over it completely without stopping. |

## ሠንጠረዥ "ለ"

### 1. በአሽከርካሪዎች የሚፈፀሙ ጥፋቶች እና የጥፋቶቹ እርከን

| ተ.ቁ. | 1ኛ እርከን የጥፋት ዝርዝር |
|---|---|
| 1 | ተሽከርካሪን ያለአግባብ የነተተ |
| 2 | የቆሟላ የጭነትማቀፊያ /ስፖንዳ/ሳይኖረው ጭነት ጭኖ ያሽከረከረ |
| 3 | የጥሩምባ ድምጽ ያለአገባብ ወይም በተከለከለ ቦታ ላይ የተጠቀመ ወይም ተገቢ ባልሆነ የማስጠንቀቂያ (የጡሩምባ) ድምጽ የቀጠቀመ |
| 4 | በመንገድ ላይ ተሽከርካሪ ያጠበ ወይም እንዲታጠብ ያደረገ አሽከርካሪ |
| 5 | በአውቶቡስ ማቆሚያ ስፍራ ላይ፣ በእግረኛ መንገድ ላይ፣ በትራፊክ ምልክት ወይም መብራት አጠገብ፣ በተሽከርካሪ መግቢያ ወይም መውጫ በር ላይ፣ ሌላ ተሽከርካሪ ደርቦ፣ ወይም በመንገድ ምልክት አማካኝነት ማቆም በተከለከለበት ማናቸውም ስፍራ ላይ ተሽከርካሪ ያቆመ |
| 6 | ከተፈቀደለት ጊዜ በላይ በማዘግየት ተሽከርካሪን በመንገድ ላይ ያቆመ |
| 7 | የአሽከርካሪውን ዕይታ የሚከለክል መጋረጃ፣ ተለጣፊ ላስቲክ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮችን በተሽከርካሪው ላይ ያስቀመጠ ወይም የለጠፈ አሽከርካሪ |
| 8 | ከተፈቀደው ፍጥነት በታች ያሽከረከረ ወይም የቀኙን ጠርዝ ሳይዝ በዝግታ ያሽከረከረ |
| 9 | የጭንቅላት መከላከያ (ሄልሜት) ሳያደርግ ወይም አድርጎ ሳያስር ብስክሌት የነዳ |
| 10 | ከመጠን በላይ ድምጽ እያሰማ ያሽከረከረ |
| 11 | የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ኖሮት ሳይዝ ያሽከረከረ ወይም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ሳያሳድስ ያሽከረከረ |
| 12 | በሕግ በተፈቀደው ርቀት ምልክት ሳያሣይ የተጠመዘዘ፣ አቅጣጫ የቀየረ፣ ተሽከርካሪ የቀደመ ወይም ተሽከርካሪ ያቆመ |
| 13 | በተሽከርካሪው ውስጥ የተሟላ የመጀመሪያ ዕርዳታ መስጫ ኪት እና የሚሰራ የድንገተኛ እሳት ማጥፊያ መሳሪያ ሳይኖረው የንግድ ተሽከርካሪ ያሽከረከረ |
| 14 | በመንገድ ላይ ያፈሰሰውን ወይም የጣለውን ፈሳሽ ወይም ጠጣርነ ገሮችን ያላነሳ ወይም ያላጸዳ አሽከርካሪ |
| 15 | በመንገድ ላይ ያለን ውሀ በተሽከርካሪው አማካኝነት በእግረኛ ላይ እንዲረጭ ያደረገ አሽከርካሪ |
| 16 | የትራፊክ ምልክት ወደቀኝ ብቻ መታጠፍ በሚፈቅድ መንገድ ላይ መንገድ የዘጋ |
| 17 | በትራፊክ መብራት ላይ ወይም በመስቀለኛ መንገድ ላይ በልመና ለተሰማሩ ሰዎች ገንዘብ የሰጠ ወይም ግብይት ያደረገ |
| 18 | የተላላፊ ሠሌዳ ከተፈቀደለት ጊዜና ቦታ ውጪ የተጠቀመ አሽከርካሪ |
| 19 | የጉዞ ረድፉን ወይም መስመሩን ሳይጠብቅ ያሽከረከረ |

## Schedule 'B'

**1. Offences Committed by Drivers and Category of Offences**

| No. | First Category of Offences |
|---|---|
| 1 | Draw Vehicle without due care |
| 2 | Drive loaded vehicle without side bar |
| 3 | Using excessive audible warning or using audible warning in a prohibited place or misuse appropriate audible warning appliance |
| 4 | Washing vehicle on road or cause washing of vehicle on road |
| 5 | Double parking or parking on the place where prohibited road signs, on bus station, on pedestrian's road, near traffic signs or traffic light or entrance or exist of vehicles |
| 6 | Parking vehicle on road in excess of the time allowed |
| 7 | Affix materials like, curtail, plastic sticker or similar things that obscure the vision of the driver |
| 8 | Drive vehicle below the allowed speed or drive slowly without taking the edge of right side |
| 9 | Ride a bicycle without wearing helmet or without tying though he wears helmet |
| 10 | Excessive voice while driving vehicle |
| 11 | Drive a vehicle without possessing driver's qualification license or without renewing driver's qualification license on time |
| 12 | Turning, changing direction, over taking vehicle or parking vehicle without showing signal at legally allowed distance. |
| 13 | Drive a commercial vehicle without equipping it with first aid kit and fire extinguisher |
| 14 | Failure to clean fluid or material he dropped on the road |
| 15 | A driver cause to sprinkle the water on pedestrian while driving vehicle |
| 16 | Closing road at a place where a traffic sign only permits right turn |
| 17 | Give money to needy people or deal with business on road light or on intersection road |
| 18 | Using a transferable plate out of permitted time and place |
| 19 | Driving a vehicle without keeping a line or lane of travel |

| | |
|---|---|
| 20 | Aboard person and load or unload freight in prohibited place or without taking right edge of road |
| 21 | Driving without light during lighting- up time while having light |
| 22 | Refuel gas on a public commercial vehicle without switch off engine while carrying passengers |
| 23 | Aboard from 1 - 3 persons in excess on a vehicle whose loading capacity of up to 25 persons |
| 24 | Aboard from 1 - 5 persons in excess on a vehicle loading capacity of more than 25 persons |

| No. | **Second Category of Offences** |
|---|---|
| 1 | Not giving priority to pedestrian or passing vehicle |
| 2 | Parking vehicle in narrow road or road turns within 12 meters |
| 3 | Drive vehicle out of category though he has a driving qualification license |
| 4 | Drive a vehicle on traffic island or drive a vehicle by crossing dispersed road island |
| 5 | Stop a damaged vehicle on road or repair a vehicle on road in excess of time allowed |
| 6 | Drive without adhering the appropriate turning direction or double turning |
| 7 | Drive ahead in the right side on two lines road |
| 8 | Drive a vehicle from parking or stop without showing the appropriate sign |
| 9 | Not giving priority to emergency service vehicle |
| 10 | Showing signal in the wrong direction |
| 11 | Unload soil, sand, stone and similar things on pedestrian road or on Vehicle road without having permission from concerned body |
| 12 | Driving a vehicle emitting or exuding smoke, gases, oil or fuel in excess of the appropriate limit |
| 13 | Driving an emergency vehicle in misappropriate use of audible warning and signals while not on emergency service |
| 14 | Drive a vehicle which aboard a minor below seven years of age without ensuring that such minor is accompanied by an adult or hugged by an instrument made for safety purpose |
| 15 | Aboard a person on the outer space of a vehicle |
| 16 | Load a freight that may cause damage to passengers |

| | |
|---|---|
| 17 | Aboard a passenger on truck in excess of legally permitted |
| 18 | Aboard in excess of more than 3 persons on a vehicle loading capacity up to 25 persons |
| 19 | Aboard in excess of more than 5 persons on a vehicle loading capacity is more than 25 persons |
| 20 | Ignore the instruction of Traffic Controller or giving wrong information or driving Vehicle by ignoring the instruction to traffic controller |
| 21 | Driving without putting a sign in case of excessive length loading freight or not properly tying or covering the freight on the vehicle |

| No | **Third Category of Offences** |
|---|---|
| 1 | Communicating through mobile telephone, or writing or sending a message or reading texts while driving a vehicle |
| 2 | Without prejudice to repairing a damaged road, driving a special vehicle which is moved with chain |
| 3 | Drive in contrary to speed law limit; or without lowering the speed in the public congestion areas, school, hospitals, intersections and pedestrians crossing road and in a prevailing weather condition that obscures the vision of the driver |
| 4 | Park a vehicle on the pedestrian crossing |
| 5 | Park on water filling fire brigade station or on hospital and fire brigade station gates |
| 6 | Drive a motorcycle without wearing helmet or wearing helmet without tying or carrying a person without making sure that a person wears and ties helmet |
| 7 | Aboard more than one person on motorcycle while driving |
| 8 | Drive a vehicle by keeping a minor under 13 years age at front sit near to a driver |
| 9 | Aboard a person on outer part of truck except appropriate permission to do so |
| 10 | Not taking care while disabled person cross a road or during aboard |
| 11 | Teach or train to drive a vehicle at a time and place not permitted to do so or without putting a sign bearing the word learner on a vehicle |
| 12 | Drive a vehicle while the door of a vehicle is open or while the door is completely not closed |
| 13 | Transfer his Driving Qualification License to other person or to a person whose Driving Qualification License is suspended in accordance with these Regulations. |

| ተ.ቁ. | 4ተኛ እርከን የጥፋት ዝርዝር |
|---|---|
| 1 | በመስቀለኛ መንገድ ላይ ቅድሚያ ሲሰጠው ለሚገባ ተሽከርካሪ ቅድሚያ ያልሰጠ |
| 2 | ተሽከርካሪው በእንቅስቃሴ ላይ እያለ ተሳፋሪ የጫነ ወይም ያወረደ |
| 3 | በሕግ ከተፈቀደው ከፍታ፣ ርዝመት፣ እና ስፋት ውጭ ጭነት የጫነ |
| 4 | ሕጋዊ ሥልጣን ሳይኖረው የትራፊክ ፍሰትን ያወከ፣ ያደናቀፈ |
| 5 | በማብሪያ ጊዜ መብራት ሣይኖረው ያሽከረከረ |
| 6 | የመለያ ሠሌዳ ቁጥሩ ሲታይ የማይችል ቦታ ላይ ያሰረ ወይም የተደመሰሰ ወይም የተቀረጠ ወይም የተሸፈነ ወይም መለያ ሰሌዳው የተለያዩ ቀለማትን የተቀባ ተሽከርካሪ ያሽከረከረ |
| 7 | በማብሪያ ጊዜ ባለ ሦስት ጎን አንጸባራቂ ምልክት በበቂ ርቀት ሳያስቀምጥ የተበላሸ ተሽከርካሪ ያቆመ |
| 8 | ቴሌቪዥን ወይም ሌሎች ምስሎችን ተሽከርካሪ ውስጥ እየተመለከተ ያሽከረከረ |
| 9 | የደህንነት ቀበቶ ሳያስር ተሽከርካሪ ያሽከረከረ |
| 10 | በ5ተኛ እርከን ከተዘረዘሩት ውጪ የሆኑ ማናቸውንም አይነት ጥፋቶችን በመፈፀም በንብረት ላይ ጉዳት ያደረሰ አሽከርካሪ |

| ተ.ቁ. | 5ተኛ እርከን የጥፋት ዝርዝር |
|---|---|
| 1 | ቀይ የትራፊክ መብራት የጣሰ |
| 2 | የትራፊክ ክብ ደሴትን በግራ ያቋረጠ |
| 3 | የትራፊክ አደጋ አድርሶ በቦታው ላይ ያልቆመ፣ ወይም ባደረሰው የትራፊክ አደጋ የተጎዳውን እና ሕክምና የሚያስፈልገውን ሰው ወደ ህክምና በመውሰድእንዲታከም ያላደረገ |
| 4 | በድልድይ ላይ ተሽከርካሪ ያቆመ |
| 5 | የፊት ወይም የኋላ ሠሌዳ ፈቶ ያሽከርካሪ |
| 6 | ስክር፣ አደንዛዥ ዕፅ ወስዶ፣ ወይም ጫት ቅሞ ወይም እየቃመ ያሽከረከረ |
| 7 | የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ታግዶበት ሳለ ያሽከረከረ |
| 8 | ማናቸውንም አይነት ጥፋት በመፈፀም በሰው አካል ላይ ቀላል የአካል ጉዳት ያደረሰ አሽከርካሪ |

| ተ.ቁ. | 6ተኛ እርከን የጥፋት ዝርዝር |
|---|---|
| 1 | ማናቸውንም አይነት ጥፋት በመፈፀም በሰው አካል ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ያደረሰ አሽከርካሪ |
| 2 | ማናቸውንም አይነት ጥፋት በመፈፀም የሰው ህይወት እንዲያልፍ ያደረገ አሽከርካሪ |

| No | Fourth Category of Offences |
|---|---|
| 1. | Not giving priority to a vehicle on cross road when to do so |
| 2 | Alight or aboard passengers while the vehicle is not at a complete standstill |
| 3 | Load a freight exceeding the legally determined height, length and width limit |
| 4 | Disturb or obstruct traffic flow without authorization |
| 5 | Drive without having light during lighting –up time |
| 6 | Drive a vehicle affix with an identification plate on obscured place or marking different colors, or affix defective or splinted plate or covered identification plate |
| 7 | Stop a damaged vehicle without putting triangular reflector sign at sufficient distance during lighting-up |
| 8 | Drive a vehicle while watching a television or other similar picture inside the vehicle |
| 9 | Drive a vehicle without tying a safety belt |
| 10 | Committing offences except those specified under fifth category and casing damage on property |

| No | Fifth Category of Offences |
|---|---|
| 1 | Contravene red traffic signal |
| 2 | Cross on the left side of traffic island circle |
| 3 | Not stopping at the place where he commits traffic accident or failure to take the person he injured to medical center |
| 4 | Stop a vehicle on bridge |
| 5 | Drive a vehicle by take off the front or the back identification plate |
| 6 | Drive under the influence of intoxication, taking drug, or chew or chewing chat |
| 7 | Drive vehicle while his driving qualification license is under suspension |
| 8 | Causes a minor bodily injury on a person by committing any kind of offence |
| **No** | **Sixth Category of Offences** |
| 1 | Causes a serious bodily injury on person by committing any kind of offence |
| 2 | Causes death of a person by committing any kind of offence |

## 2. ለጥፋቶቹ የሚቆጠር የቅጣት ነጥብ እና የቅጣት መጠን ወይም የሚወሰድ እርምጃ

### ሀ. ለመጀመሪያ ጊዜ ጥፋት ሲፈፀም

| ተ.ቁ. | የጥፋቱ እርከን | ለጥፋቱ የሚመዘገብ ነጥብ | ለጥፋቱየሚከፈል የገንዘብ ቅጣት መጠን/የሚወሰድ እርምጃ/ |
|---|---|---|---|
| 1 | 1ኛ የጥፋት እርከን | 0 | 100.00 ብር |
| 2 | 2ኛ የጥፋት እርከን | 1 | 150.00 ብር |
| 3 | 3ኛ የጥፋት እርከን | 2 | 200.00 ብር |
| 4 | 4ኛ የጥፋት እርከን | 3 | 250.00 ብር |
| 5 | 5ኛ የጥፋት እርከን | 4 | 300.00 ብር |
| 6 | 6ኛ የጥፋት እርከን - 1ኛ ተራ ቁጥር | 22 | ለስድስት ወር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይታገዳል |
| 7 | 6ኛ የጥፋት እርከን-2ተኛ ተራ ቁጥር | 28 | ለአንድ ዓመት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይታገዳል |

### ለ. ለሁለተኛ ጊዜና ከሁለተኛ ጊዜ በላይ ጥፋት ሲፈፀም

| ተ.ቁ | በጥፋቱ የሚመዘገብ ነጥብ | ለጥፋቱ የሚከፈል የገንዘብ ቅጣት መጠን |
|---|---|---|
| 1 | 2-6 | 300.00 ብር |
| 2 | 7-11 | 350.00 ብር |
| 3 | 12-16 | 400.00 ብር |
| 4 | 17-21 | ለ3/ሶስት/ ወር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይታገድና በባለሥልጣኑ የሚሰጠውን የተሀድሶ ሥልጠና እና የማሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጥ እንዲወስድ ይደረጋል |
| 5 | 22-27 | ለ6 /ስድስት/ ወር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይታገድና በባለሥልጣኑ የሚሰጠውን የተሀድሶ ሥልጠና እና የማሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጥ እንዲወስድ ይደረጋል |
| 6 | 28 እና በላይ | የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይታገዳል፤ ከአንድ ዓመት በኋላ በባለሥልጣኑ የሚሰጠውን የተሃድሶ ስልጠና እና የማሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጥ እንዲወስድ ተደርጎ ፈቃዱን መልሶ ለማግኘት ይችላል፡፡ |

## 2. ለጥፋቶቹ የሚቆጠር የቅጣት ነጥብ እና የቅጣት መጠን ወይም የሚወሰድ እርምጃ

### ሀ. ለመጀመሪያ ጊዜ ጥፋት ሲፈፀም

| ተ.ቁ. | የጥፋቱ እርከን | ለጥፋቱ የሚመዘገብ ነጥብ | ለጥፋቱየሚከፈል የገንዘብ ቅጣት መጠን/የሚወሰድ እርምጃ/ |
|---|---|---|---|
| 1 | 1ኛ የጥፋት እርከን | 0 | 100.00 ብር |
| 2 | 2ኛ የጥፋት እርከን | 1 | 150.00 ብር |
| 3 | 3ኛ የጥፋት እርከን | 2 | 200.00 ብር |
| 4 | 4ኛ የጥፋት እርከን | 3 | 250.00 ብር |
| 5 | 5ኛ የጥፋት እርከን | 4 | 300.00 ብር |
| 6 | 6ኛ የጥፋት እርከን - 1ኛ ተራ ቁጥር | 22 | ለስድስት ወር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይታገዳል |
| 7 | 6ኛ የጥፋት እርከን-2ተኛ ተራ ቁጥር | 28 | ለአንድ ዓመት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይታገዳል |

### ለ. ለሁለተኛ ጊዜና ከሁለተኛ ጊዜ በላይ ጥፋት ሲፈፀም

| ተ.ቁ | በጥፋቱ የሚመዘገብ ነጥብ | ለጥፋቱ የሚከፈል የገንዘብ ቅጣት መጠን |
|---|---|---|
| 1 | 2-6 | 300.00 ብር |
| 2 | 7-11 | 350.00 ብር |
| 3 | 12-16 | 400.00 ብር |
| 4 | 17-21 | ለ3/ሶስት/ ወር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይታገድና በባለሥልጣኑ የሚሰጠውን የተሀድሶ ሥልጠና እና የማሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጥ እንዲወስድ ይደረጋል |
| 5 | 22-27 | ለ6 /ስድስት/ ወር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይታገድና በባለሥልጣኑ የሚሰጠውን የተሀድሶ ሥልጠና እና የማሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጥ እንዲወስድ ይደረጋል |
| 6 | 28 እና በላይ | የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይታገዳል፤ ከአንድ ዓመት በኋላ በባለሥልጣኑ የሚሰጠውን የተሃድሶ ስልጠና እና የማሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጥ እንዲወስድ ተደርጎ ፈቃዱን መልሶ ለማግኘት ይችላል። |

**Demerit Points, fines and measures to be taken for Offences**

**A. For an Offence committed for the First Time**

| No | Category of Offence | Demerit points to be registered | Measures and fines |
|---|---|---|---|
| 1 | 1st Category of offence | 0 | 100.00 birr |
| 2 | 2nd Category of offence | 1 | 150.00 birr |
| 3 | 3rd Category of offence | 2 | 200.00 birr |
| 4 | 4th Category of offence | 3 | 250.00 birr |
| 5 | 5th Category of offence | 4 | 300.00 birr |
| 6 | 6th Category of offence - 1st number | 22 | license shall be suspended for 6 months |
| 7 | 6th Category of offence – 2nd number | 28 | license shall be suspended for 6 months |

**B. For an Offence committed for the Second Time and above**

| No | Demerit points to be registered | Measures and Fines |
|---|---|---|
| 1 | 2-6 | 300.00 birr |
| 2 | 7-11 | 350.00 birr |
| 3 | 12-16 | 400.00 birr |
| 4 | 17-21 | Driver's qualification certificate license shall be suspended for 3 months and the Authority shall require him to take rehabilitation training and driver's qualification approval |
| 5 | 22-27 | Driver's qualification certificate license shall be suspended for 6 months and the Authority shall require him to take rehabilitation training and driver's qualification approval |
| 6 | 28 and above | Driver's qualification certificate license shall be suspended; after a year by taking rehabilitation training and driver's qualification approval and then the Authority may grant him his driving license |

### ሐ. ቅጣትን በወቅቱ አለመፈጸምና የሚያስከትለው ተጨማሪ ቅጣት

ማንኛውም አሽከርካሪ በዚህ ደንብ መሰረት የተጣለበትን የገንዘብ ቅጣት ሳይከፍል ለሚዘገይባቸው ጊዜያት ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ በተመለከተው መሰረት ተጨማሪ የገንዘብ ቅጣትና የነጥብ ቅጣት ይጣልበታል።

| ተ.ቁ | ቅጣቱ የሚፈፀምበት ጊዜና የሚጣል ተጨማሪ የገንዘብ ቅጣት መጠን | ተጨማሪ የነጥብ ቅጣት መጠን |
|---|---|---|
| 1 | እስከ 10ኛው /አስረኛው/ ቀን ድረስ ቅጣቱን የሚፈፅም የተጣለበትን የቅጣት መጠን ብቻ ይከፍላል | 0 |
| 2 | ከ11-30 /ከአስራ አንድ እስከ ሰላሳ/ ቀናት ውስጥቅጣቱ የሚፈፅም ሰው ከ11ኛ ቀን ጀምሮ ላሉት እያንዳንዱ ቀናት የቅጣቱ መጠን 5% እየተጨመረ ይቀጣል | 2 |
| 3 | ከ30 ቀናት በላይ አዘግይቶ ቅጣቱንየሚፈፅም አሽከርካሪ ከ11ኛው ቀን ጀምሮ ላሉት ለእያንዳንዱ ቀናት የቅጣቱን መጠን 5% በተጨማሪ ይቀጣል | 3 |

### 3. ሌሎች የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

| ተ.ቁ | የጥፋቶች ዝርዝር | የገንዘብ ቅጣት መጠን |
|---|---|---|
| 1 | በማብሪያ ጊዜ በጉልህ የሚታይ መብራት ሳይዝና ለተሽከርካሪው አቅራቢያ በሆነው ጎን መብራቱን ሳያሳይ እንስሳትን የነዳ ማንኛውም የእንስሳት ጠባቂ | 100 ብር |
| 2 | ከማዘጋጃ ቤት ሠራተኞች ወይም ከተፈቀደላቸው ሰዎች በስተቀር በተሽከርካሪ መንገድ ላይ በእጅ የሚገፉ ባለመንኮራኩር ወንበርን ወይም የሚሳብ ጋሪን የገፋ ወይም የሳበ ማንኛውም ሰው | 100 ብር |
| 3 | ለመጫወቻና ለጊዜ ማሳለፊያ ተብሎ የተሰራ ብስክሌት ወይም በጫማ መልክ የሚጠለቅ ተንሸራታች ወይም ሌሎች መጫወቻዎችን በተሽከርካሪ መንገድ ላይ ያሽከረከረ ወይም የተጠቀመ ማናቸውም ሰው | 100 ብር |
| 4 | ለአሽከርካሪው ተብሎ በብስክሌቱ ላይ በተዘጋጀው መቀመጫ ላይ ተመቻችቶ ሳይቀመጥ ወይም የብስክሌቱን መሪ በሁለት እጁ ሳይዝ እና በእግሮቹም መርገጫውን ሳይረግጥ ብስክሌት ያሽከረከረማንኛውም ሰው | 100 ብር |
| 5 | ብስክሌት በሚያሽከረክርበት ጊዜ በማናቸውም አኳኋን በመንገዝ ላይ ያለ ሌላን ተሽከርካሪ ወይም ሌላን ብስክሌት ይዞ ያሽከረከረማንኛውም ሰው | 150 ብር |
| 6 | የዕድሳት ጊዜ አሳልፎ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ለማሳደስ የቀረበ አሽከርካሪ | 150ብር |
| 7 | በመንገድ ላይ እንስሳትን የነዳ ወይም ይዞ የተገኘማንኛውም ሰው | 200 ብር |
| 8 | በሕግ ሳያስፈቅድ በትራፊክ የመንገድ ምልክት የተጠቀመማንኛውም ሰው | 300 ብር |
| 9 | በተሽከርካሪ ላይ ተገቢ ያልሆነ አካል የጨመረ ወይም ከተፈቀደለት ወንበር ውጪ ተጨማሪ ወንበር ወይም መቀመጫ የጨመረ የተሽከርካሪ ባለንብረት | 400 ብር |

**C. Non-Compliance of Penalty bears additional penalty**

Any driver delays to pay fine penalty in accordance with these Regulations shall be subject to the additional penalty and demerit as described in the following schedule.

| No | Time of payment of penalty and additional fine penalty | Fine penalty |
|---|---|---|
| 1 | Up to the 10th days shall only pay the amount of fine penalty | 0 |
| 2 | Late paying the amount of fines from11-30 days starting from the 11th day the fine amount shall be increased by 5%in each day | 2 |
| 3 | Late paying the amount of fines after 30 days starting from the 11th day the fine amount shall be increased by 5% in each day | 3 |

**3. Other offences against the regulation**

| No | Offences | Fine penalty |
|---|---|---|
| 1 | Herd or lead or drive animals by herder on road during lighting-up time without carrying a clearly visible light on the side nearest to moving vehicular traffic | 100.00 birr |
| 2 | Move prams used for carrying children and smaller materials and, wheelchairs on vehicles road except workers of municipality or except authorized persons | 100.00 birr |
| 3 | Whoso ever drives or rides a vehicle or bicycle constructed and intended for play and amusement on any vehicle road | 100.00 birr |
| 4 | Whosoever rides a bicycle without firmly seated on the seat fixed on the bicycle intended for the rider or riding a bicycle Or may take his hands off from the handle bars or his feet off from the pedals while the bicycle is in motion | 100.00 birr |
| 5 | Who so ever rides a bicycle may take or hold in any manner of another moving vehicle or bicycle | 150.00 birr |
| 6 | A driver who claims to renew his/her driving qualification license after the limit period of renewal | 150.00 birr |
| 7 | Whoever rides or keeps herds on road | 200.00 birr |
| 8 | Whoever uses road sign without authorization | 300.00 birr |
| 9 | An owner of vehicle who makes additional part to the body of the vehicle (compartment) not properly or incorporate additional seating beyond the permitted limit | 400.00 birr |

| | | |
|---|---|---|
| 10 | በሐዘን ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ከሚመለከተው አካል ፍቃድ ሳይኖረው የተሽከርካሪዎችን ወይም የእግረኞችን እንቅስቃሴ የሚያውክ ቁሳቁስ ወይም ሸቀጥ በእግረኛ ወይም በተሽከርካሪ መንገድ ላይ ያስቀመጠ፣ የተከለ፣ የንግድ ሥራ የሰራ ወይም ተመሳሳይ ነገሮች ያከናወነማንኛውም ሰው | 500 ብር |
| 11 | በማብሪያ ጊዜ በጉልህ የሚታይ መብራት ሳይዝና ለተሽከርካሪው አቅራቢያ በሆነው ጎን መብራቱን ሳያሳይ እንሰሳትን የነዳ ማንኛውም የእንሰሳት ነጋጄ | 500 ብር |
| 12 | ማንኛውንም የመንገድ ምልክት ያነሳ ወይም ያበላሸ ወይም ከቆመበት ያዛወረ ወይም የለወጠ ወይም በማንኛውም አኳኋን እንዳታይ ወይም እንዳይታወቅ ያደረገ ማንኛውም ሰው | 1000 ብር |
| 13 | ያበላሸውን መንገድ መጠገኑ እንደተጠበቀ ሆነ ያለፍቃድ የተሽከርካሪ ወይም የእግረኛ መሄጃ መንገድን የቆፈረ፣ ያበላሸ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮችን ያከናወነማንኛውም ሰው | 3000 ብር |
| 14 | በባለቤትነት ወይም በይዞታው የያዘውን ተሽከርካሪ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለሌለው ሰው አሳልፎ የሰጠ ማንኛውም ሰው | 3000 ብር |
| 15 | የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳይኖረው ተሽከርካሪ ያሽከርከረማንኛውም ሰው | 5000 ብር |
| 16 | የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳይኖረው ተሽከርካሪ በማሽከርከር በንብረት ላይ ጉዳት ያደረሰማንኛውም ሰው | 7000 ብር |

4. በእግረኞች ስለሚፈፀሙ ጥፋቶችና የሚያስከትሉት ቅጣት

| ተ.ቁ | የጥፋቶች ዝርዝር | የገንዘብ ቅጣት መጠን |
|---|---|---|
| 1 | ተገቢውን ጥንቃቄ ሳያደርግ መንገድ ያቋረጠ | 40 ብር |
| 2 | ለተሽከርካሪ በተፈቀደ መንገድ ላይ ያለበቂ ምክንያት የቆመ ወይም የተጓዘ | 40 ብር |
| 3 | የእግረኛ መንገድ በሌለበት መንገድ ላይ ቀኝ ጠርዙን ይዞ የተጓዘ | 40 ብር |
| 4 | ለእግረኛ መንገድ ተብሎ ከተከለለ መንገድ ውጭ የተጓዘ | 40 ብር |
| 5 | በእግረኛ መሄጃ መንገድ ላይ ንግድ ያከናወነ ወይም ቁሳቁስ ያስቀመጠ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ለእግረኞች እንቅስቃሴ እንቅፋት የሆነ | 40 ብር |
| 6 | በብረትም ሆነ በግንብ ተለይተው የታጠሩ መንገዶች ዘሎ መንገድ ያቋረጠ | 80 ብር |
| 7 | በጆሮ ማዳመጫ የተለያዩ ድምጾችን እያዳመጠ መንገድ ያቋረጠ | 80 ብር |
| 8 | ለእግረኛ ክልክል ነው የሚል ምልክት ባለበት መንገድ ወይም እግረኛ እንዳያቋርጥ በተከለከለበት የማሳለጫ ወይም የቀለበት መንገድ ያቋረጠ | 80 ብር |
| 9 | በዚህ ሠንጠረዥ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 8 ካሉት ጥፋቶች አንዱን ፈጽሞ ክፍያ መፈጸም ያልቻለ ወይም ያልፈለገ ማንኛውም ሰው | ተመጣጣኝ የሆነ ማኅበራዊ አገልግሎት እንዲሠጥ ይደረጋል |

| | | |
|---|---|---|
| 10 | Put any material or commodity, trade, dig, damage or except mourning pitch any other thing without permit or performs similar activities that restrict the traffic on pedestrian way or vehicle road | 500.00 birr |
| 11 | Herd or lead or drive animals by trader on road during lighting-up time without carrying a clearly visible light on the side nearest to moving vehicular traffic | 500.00 birr |
| 12 | Whoever takes the road sign or brings damage to it or transfers it from the place or changes or by any means makes not visible or makes not known | 1000.00 birr |
| 13 | Subject to repairing a damaged road, discharging any other things that can damage or dig up without permit or perform any other thing on pedestrian's way or vehicles road | 3000.00 birr |
| 14 | Whosoever transfers the vehicle under his ownership or possession to a person do not have driving qualification license | 3000.00 birr |
| 15 | Whosoever drives vehicle without having driving qualification license | 5000.00 birr |
| 16 | Whosoever drives vehicle without having driving qualification license and causes damage on property | 7000.00 birr |

**4. Offences committed by pedestrian and Penalty**

| No | Offences | Fine |
|---|---|---|
| 1 | Crossing the road without due care | 40.00 birr |
| 2 | Stand or travel without sufficient reason on roads allowed to vehicle | 40.00 birr |
| 3 | Walk on the right edge of the road when there is no pedestrian way | 40.00 birr |
| 4 | Walk on a road other than pedestrian way | 40.00 birr |
| 5 | Conduct trade activity or putting any material on pedestrian road or obstruct pedestrian movement by any means | 40.00 birr |
| 6 | Cross fenced roads built by metal or brick | 80.00 birr |
| 7 | Cross the road while listening any sounds through ear phone | 80.00 birr |
| 8 | Cross intersectional road having prohibited signal for pedestrian or prohibited to cross intersectional road for pedestrian | 80.00 birr |
| 9 | Any person who violates one of offences provided under 1 to 8 of this schedule and unable to pay or refuses to pay penalty | shall be subjected to provide appropriate community service |

## ሠንጠረዥ "ለ"

## በትራፊክ ተቆጣጣሪዎች ስለሚፈፀሙ ጥፋቶችና ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

| ተ.ቁ. | የጥፋት ዓይነት | የሚወሰድ እርምጃ |
|---|---|---|
| 1 | የትራፊክ ቁጥጥር ተግባሩን ሲያከናውን ለመንገድ ተጠቃሚዎችና ለደንብ ተላላፊዎች ሙያው የሚጠይቀውን ተገቢውን አክብሮት ያላሳየ፣ ያመናጨቀ ወይም የተሳደበ፣ በማናቸውም ምክንያት አድልዎ የፈፀመ፣በዚህ ደንብ ከተደነገገው ውጪ በተለይም ጥፋተኛ ባልሆነ የመንገድ ተጠቃሚ ላይአላግባብ የደንብ መተላለፍ ቅጣትን የወሰነ እንደሆነ | አግባብነት ባለው ሕግ በዲሲፕሊን የሚጠየቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የፅሁፍ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያይሰጠዋል |
| 2 | ጉቦ የተቀበለ ወይም የጠየቀ እንደሆነ ወይም በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከላይ በተራ ቁጥር 1 ከተገለፁት ጥፋቶች አንዱን በድጋሚ የፈፀመ እንደሆነ | አግባብነት ባለው ሕግ በወንጀልና በዲሲፕሊን የሚጠየቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከትራፊክ ተቆጣጣሪነት ኃላፊነቱ እንዲነሳ ይደረጋል፡፡ |

## Schedule B

## Offences committed by traffic controller and measures taken

| No | Type of offences | Measure taken |
|---|---|---|
| 1. | Traffic controller while carrying out his duties not showing the reputation that the profession so requires, mistreats or insult or by any means commit discrimination against road user, or takes inappropriate measure not provide in these Regulation specially on road user not contravene the provision of these Regulation | Subject to the discipline measure taken in accordance with the relevant law; the last written warning is given |
| 2. | Receive a bribe or insist to get a bribe or repeatedly act within one year one of the offences described on number one | Subject to the criminal and discipline liability taken in accordance with the relevant law; removal from the position of traffic controller |

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት